የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

## *የኢሕአፓ የአውሮፓው ክፍል መደበኛ የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ*

## *መግለጫ*

ነሐሴ 16 ቀን 2006 ዓ.ም.

በአውሮፓ የኢሕአፓ ክፍል 7ኛ መደበኛ የአባላት ጉባኤ ከተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት የተወከሉ አባላቱ በተገኙበት በጀርመን ሀገር በፍራንክፈርት ከተማ ከነሐሴ 15 እስከ 16 ቀን 2006 ዓ.ም. እጅግ በተሳካ ሁኔታ ተካሄደ።

ይህ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ስኬታማነት የወደቁና የተሰዉ አባላትን የሕሊና ፀሎት በማድረግ ያስታወሰውና ለሁለት ቀናት የፈጀው ይህ ጉባኤ ከአቻው አህጉራዊ የሰሜን አሜሪካ ክፍልና እንዲሁም ከአውሮፓው የወጣት ክንፍ አካል(ወክንድ) የትግል አንድነት መግለጫ የደረሰው ሲሆን የአውሮፓው የኢሕአፓ አባላት ጉባኤ ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታ በስፋትና በጥልቀት የዳሰሰበት ነበር።

የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በጥልቀት የመረመረው ይኸው የአውሮፓው ጉባኤ ሕዝባችን ባለፉት 23 አመታት በወያኔ አገዛዝ ላይ ያካሄደውንና አሁንም በቀጣይነት እያደረገ ያለው ትግል ለዴሞክርሲ፤ ለሕግ የበላይነት፤ ለሰብአዊ መብት መከበር፤ ለእኩልነት፤ ለሀገር አንድነትና ሉአላዊነት የሚደረግ የትግል አካል መሆኑን አስምሮበታል።

ጉባኤው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሩን መቀማቱን፡ የማህበራዊ ትሥሥር ድሮቹ መበጣጠሳቸውን፡ ለከፋ የሥራ አጥነትና ድህነት መዳረጉን፡ በሕክምና እጦት ለተለያዩ በሽታዎች መጋለጡን፡ ለም መሬቶቹ ለባዕዳን በርካሽ ዋጋ መቸርቸራቸውን፡ ኑሮው መዝቀጡን፤ በአጭሩ በአስከፊ በወያኔ የባርነት አገዛዝ ሥር እየማቀቀ መገኙቱን በስፋት ቃኝቷል። በዚህም የተነሳ የሕዝብ ብሶትና ቁጣ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መምጣቱንም በመገንዘብ ድርጅታዊ ተግባራት እንዲጠናከሩ ውሳኔዎችን አስተላልፏል።

ጉባኤው እነዚህን የሥርአቱ ውጤት የሆኑትን ክስተቶች ለማስወገድ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የድርጅቱን ደካማና ጠንካራ ጎኖቹን በመገምገም በደከመበት እንዲጠናከር፡ በተጠናከረበት ደግሞ የበለጠ እንዲጎለብት የሚያስችሉ አዳዲስ እቅዶችንና የአሰራር ስልቶችን በመቀየስ በርካታ የሆኑ ድርጅታዊ ውሳኔዎችን አሳልፏል። ጉባኤው በዞናል ኮሚቴው ሥር የተቋቋሙት የተግባር ኮሚቴዎችን የሥራ እንቅስቃሴ መርምሯል። ኮሚቴዎቹ በይበልጥ ሊጠናከሩ የሚችሉበትንም መመሪያዎችን አስተላልፏል።



EPRP
P.O.BOX 73337
Washington DC, 20056
USA

Email ESPIC@aol.com
Website WWW.EPRP.com

EPRP
BP 22
92270 Bois Colombes
France

Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645

በተለይም ተኪና የወደፊቱ ሀገር ተረካቢ የሆነው ወጣት ትውልድን በተመለከተ ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶት ወጣቱን የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ በትጋት እንዲሰራ ውሳኔ አሳልፏል። ለሕዝባዊ ትግሉ ስኬታማነት መሰረት ከሆኑት የሴቶችና የተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዲጠናከሩም አስፈላጊውን ሥልት በመንደፍ አባላቱና ደጋፊዎቹ በበለጠና በተጠናከረ ዘዴ እንዲንቀሳቀሱ ውሳኔዎችንና መመሪያዎቹን አስተላልፏል። ለሰብአዊ መብት መከበር ለሚንቀሳቀሱ ተቋማት በተለይም ለኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ያለውን ከፍተኛ አድናቆት የገለፀው ይኸው ጉባኤ አባላቱ በነዚህ መስክም የበኩላቸውን እንዲያበረክቱም መመሪያዎች ሰጥቷል። ደብዛቸው የጠፋውን የኢሕአፓ አመራር ኮሚቴና የከፍተኛ እርከኖች አባላቱ የወያኔ አገዛዝ በይፋና በሕግ ፊት የት እንዳደረሳቸው እስከሚያምን ድረስ "የት ደረሱ?" ጥያቄን ያለማሰለስ በቀጣይነት እንዲስተጋባ አሳሥቧል። ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ የሚደረገው ትግልም እንዲፋፋም መመሪያዎቹን አሳልፏል። የሚያደርጋቸውን የእርዳታ ተግባርም ቀጣይነት እንዲኖራቸው ወስኗል።

በቅርቡ የወያኔ አገዛዝ በስፋት አጠናክሮ በማካሄድ ላይ ያለውን የነፃ ጋዜጠኞችንና ጠማሪያንን የማሳደድ፤ የማሰርና፤ የማፈን ዘመቻ በጥብቅ አውግዟል። እንዲፈቱም ጥሪዉን አስተላልፏል። በመጨረሻም ጉባኤው የአውሮፓውን የኢሕአፓ ክፍል ለመጪው ሁለት የሥራ ዘመን የሚያገለግሉ አዳዲስ የአመራር አባላትን በመምረጥ ተጠናቋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከጉባኤው መጠናቀቅ ማግስት በኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎቹ የተዘገጀው ሕዝባዊ ስብሰባ ከተለያዩ የአካባቢው ኗሪ የሆኑ በርካታ ወጣቶች በተገኙበት ከድርጅቱ ምሥረታ 42ኛ አመት ጋር በማያያዝ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባል የሆኑት ጓድ አቢይ ሳህሉ በእንግድነት በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል። ግንዛቤን ለመጨበጥ የሚያስችሉ ሰፋ ያሉ ውይይቶችን ያካሄደው ይኸው ሕዝባዊ ስብሰባ ተመሳሳይ ዝግጅት በቅርቡ እንደሚካሄድ በመጥቀስ የእለቱ ትዕይንት በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ
እናቸንፋለን።



**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email ESPIC@aol.com**
**Website WWW.EPRP.com**

**EPRP**
**BP 22**
**92270 Bois Colombes**
**France**

**Tel. 202 291 4217 Fax: 202 291 7645**